***የደንበኞች አገልግሎት:*** ይህ ክፍል ተጠቃሚዎች ውሃ፣መብራት እና የመሳሰሉ ግልጋሎቶችን በተመለከተ ስላሉዋቸው መብቶች ሰፋ ያለ ስልጠና ይሰጣል እንዲሁም የተጠቃሚዎችን በዋጋ ትመና ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና ይደግፋል። የደንበኞች አገልግሎት ክፍል በተጨማሪ የተጠቃሚዎችን አቤቱታ እና ጥያቄዎች ይሰማል፣ ለተለያዩ የተገልጋዮች ማህበራት እገዛ ያደርጋል፣ በተለያዩ የአካባቢ ውይይቶች ይካፈላል።.

***ኦፐሬሽን/ አገልግሎት ክፍል:*** ይህ ክፍል ቦታን የመያዝ እና የማስተዳደር ሃላፊነት አለበት። በተጨማሪም ቁሳቁስ እና የግልጋሎት መሳሪያዎች ግዢ፣የሰው ሃይል ምልመላ፣ ስልጠና እና የተለያዩ የሰራተኛ ጥቅማጥቅሞችን ያስተዳድራል።

የኦፐሬሽን ክፍል አካል የሆነው የኢንፎርሜሽን አስተዳደር ክፍል የኮምፒዩተር ሲስተምን ማሰተዳደር፣ የተ ጠቃሚዎች ስልጠና እና ድጋፍ የመስጠተ አገልግሎት እና የህዝብ መማክርት ቢሮ (ህመቢ) ድህረ ገጽን መስራት እና በየጊዜው የሚያስፈልጉ ጥገናዎችን የማድረግ ሃላፊነት አለበት።

## በጀት

የህዝብ መማክርት ቢሮ (ህመቢ) አመታዊ በጀት ለኮንግረስ ከሚቀርበው የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ካውንስል የጸደቀ በጀት ጋር አብሮ የተካተተ ነው።ማንኛውም የ(ህመቢ) በጀት ከዲሲ አጠቃላይ ገቢ ውስጥ አይመጣም።

የህዝብ መማክርት ቢሮ (ህመቢ) በሁለት የተለያዩ በጀቶች ይንቀሳቀሳል። ለእለት ተእለት ግልጋሎቶች (ለምሳሌ የቤት ኪራይ፣ደሞዝ እና መገልገያ ቁሳቁሶች) የሚውል የስራ ማስኬጃ በጀት እና ለተለያዩ የፍርድ ቤት ክርክር ላለባቸው ጉዳዮች ወጪ የሚውል በጀት። በህግ በተደነገገው መሰረት እያንዳንዱ አገልጋሎት ሰጪ ድርጅት (ፔፕኮ ፣ ቨራይዘን ፣ እና የዋሺንግተን ጋዝ ድርጅት) እና የተለያዩ የስልክ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እና በዲሲ ውስጥ ግልጋሎት የሚሰጡ የሀይል አቅራቢ ድርጅቶች የ(ህመቢ)ን አመታዊ በጀት የተወሰነ እጅ በህግ በተመደበባቸው መሰረት ይከፍላሉ። የ(ህመቢ) ከፍርድ ክርክር ጋር የተገናኘ ወጪው ጉዳዩ በሚመለከተው ግልጋሎት ሰጪ ድርጅት ይሸፈናል።

እነዚህ ሁለቱም በጀቶች በግልጋሎት ሰጪ ድርጅቶች ቢከፈሉም ቅሉ እነዚህ ድርጅቶች ለሚሰጡት አገልግሎት በሚያስከፍሉት ክፍያ ተመላሽ እንዲያደርጉ ይፈቀድላቸዋል።.ስለዚህ የ(ህመቢ) አመታዊ በጀት እና ለፍርድ ቤት ክርክር ወጪ የሚውል በጀት ከዲሲ ፍጆታ ተጠቃሚዎች እንጂ ከግልጋሎት ሰጪ ድርጅቶች ባለአክሲዮኖች አይመጣም።

## ተጨማሪ መረጃ ይፈልጋሉ?

(ህመቢ) ለዲሲ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች በሚሰጠው ሰፋ ያሉ አገልግሎቶች ይኮራል። ስለ ህዝብ መማክርት ቢሮ ማወቅ ከፈለጉ ወይም በሚቀጥለው የአካባቢ ስብሰባ ላይ ወይም በቤተክርስቲያን ፣የሰራተኛ ወይም የሲቪክ ስብሰባ ላይ የፍጆታ አጠቃቀምን በተመለከተ ንግግር የሚያደርግ ተናጋሪ ከፈለጉ ከዚህ በታች ባለው አድራሻችን ያነጋግሩን.


1133 15th Street, N.W.
Suite 500
Washington, D.C. 20005-2710
PH: (202) 727-3071
FAX: (202) 727-1014
TTY/TDD: (202) 727-2876
Email: ccceo@opc-dc.gov
Website: www.opc-dc.gov


Find us on Facebook

Revised 08/11

**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ መማክርት ቢሮ**

# ህመቢ የአገልግሎት/ፍጆ ታ ጠበቃዎት ነው





1133 15th Street, NW, Suite 500
Washington, DC 20005
Telephone: (202) 727-3071
TTY/TDD: (202) 727-2876

# የ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ መማክርት ቢሮ

የህዝብ መማክርት ቢሮ (ህመቢ) የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት ገለልተኛ የሆነ ድርጅት ነው። በህግ የድርጅቱ የህግ አማካሪዎች እና የተገልጋዮች ተወካዮች የተፈጥሮ ጋዝ፣ የሙብራት እና የስልክ ተጠቃሚ የሆኑ የዲስትሪክቱ ነዋሪዎችን ይወክላሉ። የዲሲ ህግ (ህመቢ)ን የፍጆታ አገልግሎትን በተመለከተ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን ፊት የሚቆም አካል አድርጎ ሰይሞታል። እንደዚሁም (ህመቢ) የዲስትሪክቱ ነዋሪዎችን ጥቅሞች በ ፍርድ ቤት እና በፌዴራል ተቆጣጣሪዎች ፊት ይወክላል።

(ህመቢ) ጥራቱን ለጠበቀ አገልግሎት እና በዲሲ ነዋሪዎች ዘንድ የዋጋ ተመን አድሎ እንድይኖር እና እነዚህ ዋጋዎችም ተመጣጣኝ እና ምክኒያታዊ እንዲሆኑ ይከራከራል። እንዲሁም በቢል ጉዳይ እና አገልግሎትን በተመለከተ ከካንፓኒዎች ጋር ክርክር ያለባቸውን ተጠቃሚዎች ባለባቸው ክርክር ይረዳል። እንዲሁም ለተለያዩ የአካባቢ አስተባባሪዎች እና የሲቪክ ማህበራት የቴክኒክ ድጋፍ እና የተገልጋዮች ስልጠና ይሰጣል።.

## (ህመቢ) እንዴት ሊያገለግሎት ይችላል

የዲስትሪክቱ ተመን ከፋዮችን በተለያዩ አካላት ፊት ከመወከል በተጨማሪ በሚከተሉት መልኩ ተገልጋዮችን ያግዛል

***የተገልጋዮች ቅሬታ:*** ቢሎትን እና አገልግሎትን በተመለከተ ቅሬታዎች ካሎት (ህመቢ) ሊረዳዎት ይችላል። የ(ህመቢ) ሰራተኞች እርሶን በመወከል ድርጅቱን ችግሩን በተመለከተ ቀጥተኛ ባልሆነ መልክ ለማነጋገር ዝግጁ ናቸው።. ችግሩ ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ሊፈታ ካልቻለ የፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን ፊት ሊወክሎት የሚችሉ ጠበቆችን ሊያቆምሎት ይችላል።

***የማህበረሰብ ግንኙነት:*** (ህመቢ) የማህበረሰቡን በህግ አስከባሪነት ሂደት ተሳታፊነት ያበረታታል። እንዲሁም ለዲሲ ነዋሪዎች የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል እና መረጃ ይሰጣል።.የ (ህመቢ) ሰራተኞች በ (ANC) ኤንሲ፣ ሲቪክ ማህበራት፣ እና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በተለያዩ የማህበረሰብ ስብሰባዎች ማህበረሰቡን በወቅቱ የፍጆታ አጠቃቀሞች ዙሪያ ንግግር ያደርጋሉ።.እንዲሁም (ህመቢ) የኮንሲዩመር ዩቲሊቲ ቦርድን ጨምሮ ለተለያዩ የዲሲ የአካባቢ አስተባባሪዎች እና የሲቪክ ማህበራት የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል።. ሰራተኞቻችን መጥተው ንግግር እንዲያደርጉ ከፈለጉ .የ(ህመቢ)ን የደንበኞች አገልግሎት ክፍልን ስብሰባው ሊደረግ ሁለት ሳምንት ሲቀረው ያነጋግሩ።

***ጽሁፎች:*** ህዝቡ ስለ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች፣ የተጠቃሚ መብት ጉዳይን በተመለከተ እና በሙግት ላይ ያሉ ጉዮችን የደረሱበትን ለማሳወቅ (ህመቢ) የመረጃ ጽሁፎች፣ ትራክቶች እና ሌሎች ጽሁፎችን ያሳትማል። የ(ህመቢ) የማስተማር እና የማህበረሰብ ግንኙነት ተግባራት በድህረ ገጹ ላይ እና ፌስ ቡክ በሚሰጠው መረጃ ይታገዛል, www.opc-dc.gov እና Facebook.። በተጨማሪም (ህመቢ) ስለሚሰጠው አገልግሎት ህዝቡን ለማስታወቅ (ህመቢ) የተጠቃሚዎች ቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የጋዜጣ ጽሁፎች እና ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ይጠቀማል።

## የቢሮው ታሪክ

(ህመቢ) በመጀመሪያ በ 1926 በዩናይትድ ስቴትስ ኮንግረስ ከተቋቋመ በኋላ በኮንግረስ በፌዴራል መንግስት መልሶ የማዋቀር ሂደት ወቅት በ 1952 ተዘግቶ ነበረ። በ1975 በነበረው ከፍተኛ የኢነርጂ ዋጋ መጨመር ምክንያት እንደገና በኮንግረስ ተቋቁሞዋል።. ቢሮው የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት ገለልተኛ የሆነ ድርጅት ሆኖ በ ጃንዋሪ 2፣1975 ተቋቁሞዋል።

## ድርጅታዊ መዋቅር

(ህመቢ) በ2011 በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስምምነት እና ምክር በከንቲባ ቪንሰንት ሲ ግሬይ በተሾሙት በህዝብ መማክርት ጠበቃ ሳንድራ ማታቮስ-ፍራይ ን የመራል።

***ዳይሬክተሮች:*** የህዝብ መማክርት ቢሮ የድርጅቱን የእለት ተእለት ስራ ይመራል፣ የገንዘብ በጀቱን ያቅዳል ያስተዳድራል፣ ድርጅቱን በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን ፊት፣ በኮንግረስ ፊት ይወክላል። እንደዚሁም በድርጅቱ ተልእኮ መሰረት ፖሊሲ ያረቃል እንዲሁም ይተገብራል ።

***የፍርድ ክርክር አገልግሎት:*** ይህ ክፍል ለዲሲ ተገልጋቶች ፍጆታ አገልግሎት ሰጪ ካንፓኒዎችን በተመለከተ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን ፊት፣ በፌዴራል ህግ አስፈጻሚዎች ዘንድ ይቆማል ።እንደዚሁም (ህመቢ) የዲስትሪክቱ ነዋሪዎችን ጥቅሞች በ ፍርድ ቤት እና በፌዴራል ተቆጣጣሪዎች ፊት፣ፌዴራል ፍርድ ቤቶች፣ እና በዲሲ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይወክላል። እንዲሁም ወደ ፍርድ ቤት ክርክር ለሚሄዱ ጉዳዮች የመከራከሪያ ስትራቴጂ ማዘጋጀት እና በዚህ ጉዳይ የሚሳተፉ የሙግት ቡድን አባላትን ማለትም የድርጅቱን ሰራተኞች እና ከውጪ የሚመጡ አማካሪዎችን እና የባለሙያ ምስክርነት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ያቀናጃል።